እንብበው ያስነብቡ !

# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤ቁጥር 3 ግንቦት 21 2000 ዓ.ም

www.ginbot7.org

## ግንቦት 20ን ስናስታውስ ለገዢዎቻችን ፈንጠዝያ ለኛ ሃዘን - ለምን?

ሰሞኑን የመለስ አታሞ የግንቦት 20ን 17ኛ አመት የድል በአል ይደልቃል :: የኢኮኖሚ ዕድገቱ ፣ የፍትህ ምጥቀቱ ፣ የብሄር እኩልነቱ ፣ አፍሪካን እያስከነዳ መሆኑና፣ ለአለም የልማት ተኮር መንግስታት ምሳሌነቱ ይፎከራል :: «ሆኖን ነው !» ይላል የጎንደር ሰው ፣ ፉከራው ከጀግንነቱ ሳይገጥም ፣ ተስፋው ከሃቁ ሳይበራይ ሲቀር :: እኛም «ተገኝቶ ነው ወይ» ብለን እንደየችሎታ እንዳቅማችን መለከትና እምቢልታውን ይዘን ለብቻው የሚጮኸውን ከበሮ በተቀላቀልን ደስ ባለን ነበር :: ሆኖም የኢትዮጵያ ህዝብ ህይወት ከምጣዱ ወደ እሳቱ እየተገላበጠ ማረሩን ፣ በቀን ሁለት ከመብላት ወደ አንድ መውረዱን እንጂ ፣ አታሞው እንደሚደሶክረው በሚሊዮን የሚቆጥሩ ገባሮችን አላየንም ::

ለምን የገዢዎቻችን ተስፋ አይነዝረንም? ለምን የደስታቸው ተካፋይ ለመሆን አቃተን? ብዙ ምክንያቶችን ማቅረብ ይቻላል ፤ ለዚህ እጥር ምጥን ላለ መጣጥፍ ግን የሚቀጥሉት በቂ ናቸው :: ባለፉት 17 የግፍ አመታት ፤ ሃገራችን ኢትዮጵያ የብሄረሰቦች እኩልነት ካልነበረበት የደርጉ ዘመን ፣ ዘረኛ አገዛዝ ህጋዊ ወደሆነበት ጨለማ ተሸጋግራለች :: ብሄ ረሰቦች በቋንቋቸው ለምን ከባቢያቸውን አስተዳደሩ ፣ ለምን ባህላቸውን አሳደጉ ብለን አይደለም «ዘረኛ አገዛዝ ወደሰፈነበት ጨለማ ተሸጋግረናል» የምንለው :: በክልል አስተዳደር ስም ከቀበሌ እስከ ካቢኔ ፣ የከባቢያቸውን ህዝብ አቅምም ሆነ ተስፋ የማይመጥኑ ተራ ዱርዬዎች በገዢነት የተ ሰየሙበት «ፌዴራሊዝም» በመሆኑ እንጂ ነው :: ተጠሪነታቸውም ለከባቢያቸው ህዝብ ሳይሆን ፣ በምግባረ ብልሹነታቸውና ድንቁርናቸው የበላይነት ያገኙትን እየመረጠ ለሥልጣን ያበቃቸው የበረከተ-መለስ ማፊያዊ ማእከል መሆኑን ስለምናውቅም ጭምር ነው :: በዱርዬዎች መሪነት ፌዴራሊዝምም ሆነ ልማት እንዳይኖር እናውቃለንና ነው ደስታቸው ደስታችን መሆን ያልቻለው:: ሌላም ምክንያት አለን :: ኢትዮጵያችን ከዳኛ ፊት ባለጉዳይ ከመቅረቡ በፊት በጉልበተኞችና መልከኞች ፣ በጉልተኞችና ወታደሮች ሰው አበሳውን የሚያይባት ሃገር ነበ ረች :: *ወደ ገጽ 3 ዞሯል፤*

### የኢትዮጵያ የጠበቆች መሃበር ተለጣፊ ሊበጅልት ነው::

ተለጣፊዎች በማቆም የታወቀው የመለስ፣ የበረከትና የስብሃት የማፍያ ቡድን አዲስ ተለጣፊ ለማቆም ሽር ጉድ እያለ ነው፡ ያሁኖቹ ባለተረኞች ደግሞ የሃገሪቱ የህግ ባለሙያተኞች ጠበቆች ናቸው:: ጠበቆች በፍላጎታቸውና በነጻነት ያቆሙትን ማህበር ህልውና አጥፍቶ በወያኔ ኢህአዴግ አምሳል በተፈጠረ በሌላ ተለጣፊ ድርጅት ለመተካት ሴራው ተጀምሯል:: አገዛዙ የጠበቆችን ማህበር አላውቅም፣ የማህበሩ ፈቃዱ እንዲታደስ አልፈቅድም እያለ ነው:: በቅረቡ ይህንን ጉዳይ በሚመለከት በመለስ ዜናዊና በ አድርባይነት መመዘኛ በተመረጡ ጠበቆች መሀል ወይይት ተደርጎ ነበር:: ይህ ወይይት የወቅቱን የጠበቆች መሃበር ፕሬዚዳንት አቶ ታምሩን ያገለለ፤ ለአገዛዙ ያደገደጉ እንደ ሚሊዮን አሰፋ፣ የመለስ ዜናዊና የህወሃት የግል ጠበቃ የሆነውን መብረሃቱ ዮሃንስንና ሌላ ለወያኔ-ኢህአዴግ ነፍሱን ለመሸጥ የተዘጋጀ አጎብዳጅ ማርቆስ የሚባል ጠበቃ የተሳተፉበት መሆኑ ታውቃል:: *ወደ ገጽ 2 ዞሯል፤*

### መለስ ዜናዊ ከ300 በላይ ከሚሆኑ ከግብረሰናይ ድርጅቶች ተወካዮች ጋር ስብሰባ አደረገ:: ስብሰባው ብዙ ጉድ የታየበትና የተነገረበት ነበር::

እሁድ ግንቦት 17 2000 ዓ.ም መለስ ዜናዊ ከ300 በላይ ከሚሆኑ የግብረሰናይ ድርጅቶች ተወካዮች ጋር በጽ/ቤቱ አዳራሽ ስብሰባ አደረገ:: የስብሰባው አለማ የግብረሰናይ ድርጅቶን አጠቃላይ እንቅስቀሴ ለማፈን ሲባል በወጣው

## «ሕጋዊ» ዘረፋ፤ የሽፍቶች ካፒታሊዝም በኢትዮጵያ::

ብርሃኑ ነጋ

በበአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያችን የሚሰማው ኢኮኖሚ ነክ ወሬ በጣም እርስ በእርሱ የሚጋጭ ስለሚመስል ጉዳዩን ለሚከታተል ሰሚ እጅግ ግራ ቢያጋባው የሚያስገርም አይደለም:: የኢትዮጵያ መንግስት በታሪክ ታይቶ ስለማይታወቀው ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት በየጊዜው የሚደሰኩረው ፕሮፓጋንዳ፤ ለጉብኝት ወደ አዲስ አበባ ሄደው የሚመጡ ኢትዮጵያውያን ስለአዲስ አበባ አስደናቂ እድገትና ስለ ፎቆችና መንገዶች መሰራት የሚያወሩት ወሬ፤ በቅርቡ የአለም የገንዘብ ድርጅት ስለ ኢትዮጵያ ያወጣው አወንታዊ የኢኮኖሚ ዘገባና ተመሳሳይ አወንታዊ ዘገባዎች በአንድ በኩልና፤ በእለት ተቀን ከነዋሪው ህዝብ ከምንሰማው «እንዲህ አይነት አስከፊ ኑሮ በታሪካችን አይተን አናውቅም » ምሬት፤ በአገሪቱ ረሀብ ስለ-መግባቱ በምስል እየተደገፈ ከሚቀርበው ዜና ጋር ፍፁም የሚጣጣም አይደለም:: በመንግስት በኩል የሚወራውን ወሬ እንደ ዘወትር ውሸታቸው አቃለን ብናልፈው እንኳዋን ከሌሎቹ የሚሰማው ወሬን ዝም ብለን ልናልፈው አንችልም:: ቢያንስ ነገሩን ለመረዳት መጣር፤ ተ ረድቶም ላይ ላዩን ከሚታየው ውስጥ ገብቶ የሚሆነውን ነገር ማወቅ የአመለካከት ጥራት ይሰጠናል:: ለዴሞክራሲ ትግሉም እጅግ ጠቃሚ ነው:: በዚህ ላይ የግንቦት 7 ድምፅ አትኩረት ሰጥቶ ወደፊት ተከታታይ ፅኑፎች ያስነብበናል በዬ እጠብቃለሁ:: በዚህ አጭር ጽሁፍ የአገሪቱን ኢኮኖሚ አጠቃላይ ገፅታ ወይንም ደግሞ እነኝህን የተጣረሱ መረጃዎች ሙሉ ለሙሉ ለመፍታት የሚያስችል ትንተና ለመስጠት አልታሰበም፤ ቢታሰብም የሚቻል አይደለም:: የፅሁፉ አላማ በጣም ጠባብ ግን በእኔ እምነት አስፈላጊ ነገር ነው:: በኢኮኖሚው ዙሪያ የሚካሄደውንና በጣም ዘላቂ የሆነ እንድምታ ያለውን አንድ ክስተት ብቻ በመመልከት የነገሩን አደገኛነት ለማሳየትና የህዝቡንና ለዴሞክራሲ የሚታገለውን ሀይል ቀልብ ወደዚያ እንዲያነጣጥር ለማመላከት ብቻ ነው::

**በመጀመሪያ ብዙ በማያጣሉት ሶስት እውነታዎች ላይ እናተኩር::**

በእርግጥም በአዲስ አበባ ብዙ ህንፃዎች ይሰራሉ፤ ህንፃዎቹም እንደ ከዚህ በፊቱ በቁጥቁጥና ብዙ ገንዘብ ላለማውጣት በመጠንቀቅ የሚሰሩ ሳይሆኑ በተወሰነ ደረጃ ዘመናዊ የሆኑ፤ ለማሳመር የሚወጣ ወጪ ላይ ቸር የሆኑ ትላልቅ ህንፃዎች ናቸው:: ይህም ማለት ባለቤቶቹ ወይንም በጣም ብዙ ብር ያላቸው ናቸው፤ አለያም ገንዘብ በቀላሉ የሚያገኙበት ምንጭ አላቸው:: *ወደ ገጽ 4 ዞሯል*

# ርእሰ አንቀጽ

## ህዝብ የሃገሩና የመንግስት ስልጣን ባለቤት ሳይሆን ብሄራዊ ደህንነትና ብሄራዊ ጥቅም ሊከበር አይችልም።

ሰሞኑን ከህዝብ ጀርባ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ የተካሄደው ሃገራዊ ክህደት የመጀመሪያውም የመጨረሻውም አይሆንም። በብሄራዊ ደህንነትና ጥቅም ላይ የሚሰነዘር ጥቃት ለሱዳን የኢትዮጵያን መሬት አሳልፎ በመስጠት፣ ሃገሪቱን ያለባህር በር በማስቀረት፣ ሱማሊያን ወሮ ግፍ በመፈጸም መውጫ በሌለው ጦርነት ውስጥ ገብቶ የሃሪቱን ዜጎችና ሃብት መማገድ፣ ከሲያድ ባሬ ውድቀት በኋላ ከኢትዮጵያ ወገኑ ጋር መቀራረብ ጀምሮ የነበረውን የሶማሊያ ህዝብ በሃገራችንና በህዝባችን ላይ ለረጅም ግዜ የማይጠፋ ምሬትና ቂም እንዲቋጥር በማድረግ ብቻ የሚገለጽ አይደለም።

እነዚህ ትልልቅ ጉዳዮች በቀጥታ ከሌሎች መንግስታት ጋር የሚገናኙ በመሆናቸውና በተለምዶም የክህደት ወንጀሎች ብለን በምናውቃቸው ጸረ-ሀገር ድርጊቶች ስር ስሚጠቃለሉ ጎልተው ይታያሉ። በሌላ በኩል፣ በአንድ ልኡላዊ ሃገር ውስጥ የሚገኝን ህዝብ በዘር ከፋፍሎ፣ በሃገር ላይ የሚደርስን ጥቃት በሁሉም ዜጋ ላይ እንደደረሰ አደርጎ ህዝብ እንዳያይ የሚያደርግ ዘረኛ የአገዛዝ ስርአት መዘርጋት ብሄራዊ ደህንትና ጥቅም ይጎዳል። ሃገራዊ ክህደት ነው። የአንድ ሃገር ህዝብ የመናገር የመሰብሰብ የመደራጀት መብቱን ገፎ በሃገሩ ባበርነት እንዲኖር በማድረግ ህዝብ ስለሃገሩ ጥሩ ስሜት እንዳይኖረው የሚያደርግ፣ በሃገሪቱ መናገሻ ከተማ የሃገሪቱ ተረካቢ የሆነው ወጣት ትውልድ "ከወያኔ ይሻላል ሱማሌ" የሚል መፈክር እንዲያሰማ የሚያደርግ  የፖለቲካ ስርአት ብሄራዊ ጥቅምንና ደህንነትን ይጎዳል። ይህም ሃገራዊ ክህደት ነው። ዜጎች መብታቸው ተከብሮ ተረጋግተው የሚሰሩበትን ሁኔታ በማሳጣት ሀገሪቱ በከፍተኛ ድካም ያስተማረቻቸው ምሁራን በገፍ እንዲሰደዱ በማድረግ, በእውቀት ላይ የተመሰረተ ፈጣን የእድገት ለውጥ ሃገራችን ማድረግ የምትችልበትን መንገድ መዝጋት ብሄራዊ ጥቅምንና ደህንነትን ይጎዳል። ይህም በሀገር ላይ ክህደት መፈጸም ነው። በሃገራቸው የልማት ስራ ለመስራት የሚያስቡትን ባለሃብቶች፣ሁሉም በእኩልነት የሚወዳደሩበትን የኢኮኖሚ መስክ እንዳይኖር በማድረግ፣ በአድሎና በዝምድና ላይ የተመሰረተ፣ ጥረትና በጥረት የሚመጣ ተሸላሚነትን የዘጋ የኢኮኖሚ ስርአት በመፍጠር የባለሃብቶችን ተስፋ ማቀጨጭ፤ ራሰቸውን ጠቅመው ሃገራቸውን መጥቀም በሚችሉባቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች በልበ ሙሉነት እንዳይሳተፉ ማድረግ ብሄራዊ ጥቅምንና ደህንነትን ይጎዳል። ይህም የክህደት ወንጀል ነው። ተደጋግሞ ተደጋግሞ በአፍሪካ አምባገነኖች ተሞክሮ የወደቀን፣ ለአምባገነኖቹ የገነት ህይወት የከፈተ፣ ለህዝባቸው ግን ሃገራቸውን ሲኦል ያደደረገ፣ በየሃገሩ የዘር ጦርነት በመቀስቀስ በሚሊዮኖች ህዘብ እንዲተላለቅ ያደረገ፣ ‹የልማት መንግስት› የሚባል የመንግስት ስርአት የሚያሞካሽ የቀጣፊዎች ፖሊሲ በሃገር ላይ ለመጫን የሚደረገው ሽር ጉድ፣ በሃገራችን ረሃብን ማሰቆም፣  ድህነትን ማጥፋት ሰላምና መረጋጋት ማምጣት፣ በሃገራዊ አርበኛነት ዙሪያ በእኩልነትና በአንድነት የሚኖሩ ዜገችን ማፍራት የምንቸልበትን ወርቃማ ግዜ የሚያባክን ነው። ይህም እንደ ሃገርና አንደ ህዝብ ብሄራዊ ደህንነታችንና ጥቅማችንን ለመከላከል ያለን አቅም የሚቦረቡር ነው። ይህም የክህደት ወንጀል ነው።

## የኢትዮጵያ የጠበቆች መሃበር ተለጣፊ ሊበጅልት ነው፡፡

መለስ ዜናዊ ጠበቆች ለተቃዋሚው ጥብቅና በመቆም እራሳቸው ተቃዋሚ መሆናቸውን አሳይተዋል በሚል ቂም ተገፋፍቶ ድርጅታቸውን ከላይ በተጠቀሱ ግለሰቦች በሚመራ ተላፊ የጠበቆች መሃበር ሊተካ መቁረጡን ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡ የመለስ የማፍያ ቡድን ስልጣን ከመያዙ በፊት ብአዴን አሆዴድ የሚባሉ የኢህአዴግ ተለጣፊ ድርጅቶች መፍጠሩን፣ ነጻ የጋዜጠኖች፣ የመምህራንና የሰራተኞች ማህበራትን በማፍረስ በምትካቸው ተለጣፊ መሃበራት መፍጠሩን፣ ከእዛም አልፎ እውነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በማጥፋት የራሱን ተለጣፊ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በማቆም እስካሁን ያለምንም ሃፍረት የፈጸመውን ድርጊት በጠበቆች ላይ ቢደግመው የማያስገርማቸው እንደሆነ የሚፈጸመው በደል ያንገበገባቸው የህግ ባለሙያተኖች ለግንቦት ዜና አስረድተዋል፡፡

**በሃገራችን ላይ የመፈጸመውን የክህደት ወንጀል፣ በንብረታችን ላይ የሚፈጸመውን ዘረፋ፣ በመብታችን ላይ የሚጫነውን አፈና ለማስቆም፣ በአንድነት እንነሳ። አሻፈረኝ! በቃኝ! በመለስ አገዛዝ ላይ አንበል**

## መለስ ዜናዊ ከ300 በላይ ከሚሆኑ ከግብረሰናይ ....

በእዚህ ስብሰባ ላይ መለስ ዜናዊ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችን በሁለት በመክፍል፣ በሰብአዊና የሲቪል መብቶች፣ በመልካም አስተዳደር፣ የህግ የበላይንትና በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ የሚሰሩትን ግብረ– ሰናይ ድርጅቶች፣ የእርዳታና የልማት ስራ ከሚሰሩ ድርጅቶች በመለየት የመጀመሪያዎቹ ምንም ስራ እንዳይሰሩ፣ በሀገር ወስጥ መንቀሳቀስ እንዳይቸሉ የሚያደርገውን ህግ ትክክለኛነት ለመግለጽ ሙከራ አድርጓል።

መለስ ዜናዊ ፣ሰብአዊና ዴሞክራሲ መብቶችን በሚመለከት ትምህርትና ስልጣና የሚሰጡትን ግብረሰናይ ድርጅቶች፣ ስራቸው ወገንተኛ የሆነ የፖለቲካ ስራ ስለሆነ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ለይቶ እንደማያያቸው ተናግሯል፡፡ በእዚህም የተነሳ ከ10 በመቶ ከሚሆነው፣ ወደ ውጭ ለመጓጓዣና ስብሰባ ለመካፈያ ከሚገለገሉበት ገንዘብ ውጭ ምንም አይነት ተጨማሪ ገንዘብ ከህገር ውጭ መቀበል እንደማይችሉ ገልጧል፡፡ በእዚህ ስብሰባ ላይ ከታዩት ጉዳዮች መሃል አንዱ እንደማናቸውም ሁሉን አውቃለሁ እንደሚሉ አመባገነኖች መለስ ዜናዊ በማያውቀው የህግ ሙያ ገብቶ ከህግ አኳያ ሲያቦካ መዋሉ ነው፡፡

ይህ ግለሰብ በውጭ ሃገር እርዳታ ለሰብአዊና ለዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከራከሩ ድርጅቶን ካገር ለማጥፋት ያቀረበው ዋንኛ መከራከሪያ በፖለቲካ የዜግነትና በህግ የዜግነት መብት መሃል ያለውን ልዩነት የማያውቅ፤ ስልጣን ብቻ ስላለው ሁሉንም ነገር የሚችል የሚመስለው ግብዝ መሆኑን ያሳየበት ነው፡፡ መለስ  ህግ አዋቂ ሆኖ ባቀረበው ክርክር ‹ግለሰቦች እንጂ ድርጅቶች የዜግነት መብት የላቸውም በመሆኑም በህግ መንግስቱ የተቀመጠው የዜግነት መብት ለእነሱ አይሰራም፡፡ በመሆኑም ህገ መንገስታዊ መብት የላቸውም›› የሚል ነበር፡፡ ከእዚህ ተነስቶ የወጣው ህግ ህገ-መንግስቱን የጣሰ ነው የሚል ክርክር ማንሳት አይቻልም የሚል ነው፡፡ የሚገርመው ግን ግብረ ሰናይ ድረጅቶቹ ያቀረቡት የመብት ክርክር በዜግነትና በዜግነት የፖለቲካ መብት ላይ ሳይሆን  ማንኛውንም ሃገራዊ ድርጅት ህጋዊ መብት በሚሰጠው የሃገሪቱና የአለም አቀፍ ህገመንገስቶችና ስምምነቶች ላይ በመመስረት ነበር፡፡ ሀገራዊ ህጋዊ ሰውነት፣ ህገ መንግስታዊ መብትና ግዴታ በግልጽ በተደነገገበት ሃገር ግብረሰናይ ድርጅቶች ይህን ህገ-መንግሰታዊ መብታቸውን የጣሰ ስራ መንግስት ሊሰራ አይገባውም ነበር ያሉት፡፡ ህጋዊ ሰውነት ያላቸውና እንደ አንድ አካል ተወሰደው ሊከሱና ሊከሰሱ የሚችል መብት ያላቸውን ድርጅቶች ህገ መንግስቱን በሚቃረን ሌላ ህግ መብታቸውን መግፈፍ እንደማይገባ ለመግለጽ የግብረ-ሰናየይ ድርጅቶቹ ያደረጉት ሙከራ የትም አልደረሰም፡፡ በሌላ በኩል ግን የመለስ አላማ በሀገራችን ያሰፈነውን አምባገነናዊ አንድ ፓርቲ አገዛዝ በማንኛውም መንገድ ሊፈታተኑ የሚችሉ ማናቸውን ቡድኖች፣ የፖለቲካም ይሁኑ የግብረሰናይ ድርጅቶች እያነፈነፈ ለማጥፋት ከጉልበት ጀምሮ የህግን ከላላ በመጠቀም ወደ ኋላ የማይል መሆኑን በስብሰባው ላይ ታይቷል፡፡ የውጭ መንግስታት ህግን፣ ሰብአዊ መብትንና መልካም አስዳደርን በሚመለከት የሚሰጡት የገንዘብ እረዳታ በራሱ በአገዛዙ እውቅና የሰጣቸው የራሱ ተለጣፊ የሙያ ማህበራት ፤ የሴቶች የወጣቶች የብዙሃን ማህበራት ብቻ እንዲሆኑ ተደርጎ የተዘጋጀ ህግ እንደሆነ ግልጽ ሆኖ ወጥቷል፡፡ የውጭ መንግስታት የእርዳታ ድርጅቶች አንዲህ አይነቱን አይን ያወጣ የአንድን አምባገነን ፓርቲ ፍጹማዊ ቁጥጥር ለሚያጠናክር ሴራ ተባባሪ ይሆናሉ ብሎ ማሰብ ባይቻልም በተለያዩ ሃገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ይህንን በያሉበት ለሚገኙ የመንግሰት ባለስልጣናት በማስረዳት የመለስ ዜናዊ መንግስት ከእነዚህ መንግስታት ትብብር እንዳይደረግለት ዘመቻ ማድረግ እንዳለባቸው በስብሰባው ሂደትና በመለስ ዜናዊ እብሪት የተናደዱ የስብሰባው ተሳታፊዎች ጥሪ አቅርበዋል፡፡ ወደ ገጽ 3 ዞሯል፤

**አዘጋጆች**

ፋሲል የኔአለምና እና ደረጀ ሃ/ወልድ

**የፖስታ ሳጥን ቁጥር**
POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands



**የግንቦት ሰባት ድምጽ ጋዜጣ የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፡ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ አቶ መሰፍን አማን፤አቶ ቸኮል ጌታሁን፤ሁሉም የቅንጅት ለአንድነትና  ዴ ሞክራሲ ፓርቲ የላእላይ ምክር ቤት አባላት  የነበሩ።

ሆኖም ዳኛ ፊት የቀረበ ዜጋ በህጉ እንዲዳኝ ቢያንስ ተስፋው የነበረበት ዘመን ነበር ። ባህሉን ፣ ወጉን ፣ ዕምነቱን የሚያውቁ ዳኞችም ይሠየሙ ነበር ። ባለፉት 17 አመታት ግን ፣ ህዝብ «የድንጋይ ፋብሪካ» ብሎ ከሚጠራው የካድሬ ኮሌጅ የተመረቁ የዘረኛው ስርአት አፋሽ አጎንባሾች ፣ «ዝለል» ሲባሉ «ምን ያህል?» የሚሉት ደካሞች ብቻም እየተመለመሉ በዳኝነት ስም የተጎለቱበትና፣ ፍትህ መሳቂያ መሳለቂ ፣ ዳኝነትም የጠሉትን ማጥቂያ መሳሪያ መሆኑ ፀሃይ የሞቀው ጉዳይ ነው ። በህዝብ የተመረጡ እንደራሴዎች «በዘር ማጥፋት» ወንጀል የሚከሰሱበት ፣ የኢትዮጵያን ጨለማ በተስፋ ብርሃን ለማላበስ በህሊናቸው ሃይል አምጠው የወለዱ ተዎድሮሶች በተልካሻ ክስ የሚንገላቱበት ፤ ሥራቸው የሚጠይቀውን ተግባር በመፈፀም ለነጋዴዎች ብድር የሰጡ የባንክ አስተዳዳሪዎች ያለመረጃና ክስ ለአመታት በወህኒ የሚሰቃዩበት ፣ ይህ ነው የ17ቱ አመታት የበረከተ-መለስ ፍትህ ። በዚህ እንድንደሰት እንዴት ይጠበቅብናል?

ሌላም እናክል ። ለሃገር ብሄራዊ ጥቅም አለመቆም ፣ የሃገርን ዳር ድንበር ማስደፈር ፣ የታሪካዊት ኢትዮጵያን ድንበሮች ለድርድር ማቅረብ ፣ ኢትዮጵያን ያለባህር በር ለመቆለፍ መቅበዝበዝ ፣ ይህ ነው የነዚህ 17 አመታት አገዛዝ ትርፍ ። የሃገሩን ዳር ድንበር መጠበቅ ተግባሩ የነበረውን የመከላከያ ሠራዊት አፈናቅሎ ፣ የጎረቤት ሃገር እንዲወር ማድረግ ፣ የተረፈውን ደግሞ በራሱ ህዝብ ላይ እንዲዘምት በ«መጡብህ» ዘረኛ ቅስቀሳ ማስበርገግና በወንጀላቸው እንዲተባበር ማድረግ ፤ ይህንንም ለማሳካት እንዲያስችላቸው ፤ በስየ አብርሃ ዘመን ጀምረውት የነበረውን የሠራዊቱን የብሄረሰብ ተዋፅኦ ማስተካከል ሥራ እርግፍ አድርጎ መተው ብቻ ሳይሆን ፤ ከግንቦት 97 ምርጫ ሽንፈታቸው በኋላ ይብሱኑ ብለው የኦሮሞና አማራ የጦር መኮንኖችን ከሠራዊቱ በማግለልና በቁጥጥር ሥር በማዋል ፤ ለደረጃ ዕድገትም ከችሎታና የጀግንነት ፍፃሜ ይልቅ ታማኝነትና ዘረኝነት ዋናው መለኪያ የሆነበት ፤ ይህ ነው ያለፉት 17 አመታት የበረከት-መለስ የሀገር መከላከያ ግንባታ ።

የዛሬ 17 አመት በቁምጣ ሱሪና በረባሶ ጫማ ከመዲናችን የገባው የኢህአዴግ ሠራዊት ቆም ብሎ «ያ ሁሉ መስዋእትነት ለምን ነበር?» ብሎ ራሱን ሲጠይቅ ያገኘው ውጤት ከከፈለው መስዋእትነት ጋር የሚመጥን ሳይሆን ፤ ጓዶቹ የነበሩ መሪዎቹ ወደ ገዢነት የተለወጡበት ፤ የነርሱንም የቅምጥል ኑሮ ለመንከባከብና የግፍ አገዛዛቸው በየማእዘኑ የቀፈቀፋቸውን የትጥቅ ትግሎች ለመቆጣጠር ሠራዊቱን በህዝብ አፈናና ጭፍጨፋ ያሰማሩበት ፤ ሁርሶ ባገኙት «ዘመናዊ» ወታደራዊ ሥልጠና ላይም ተመሥርተው ፤ በኦጋዴን ህፃናት ላይ ግብረ ሶዶም እስከመፈፀም የደረሱበት ፤ የደርጉን ዘመን ጭካኔ ባለፈ ፤ ኢትዮጵያዊ ሥነምግባርን ወጊድ ያለ ብልግና የሚፈፅም ሠራዊት እንዲሆን እየተደረገ ባለበት ሰአት ነው ሠራዊቱ የግንቦት 20ን 17ኛ አመት የግፍ አገዛዝ የሚያከብረው ። በነዚህ ሁሉ አሳፋሪ ፍፃሜዎች ያዘኑ የጦር መኮንኖች «እረ የሰሚ ያለህ ፤ ከደርጉ ባስን» ብለው እስከመናገር መድረሳቸውንም የምናውቀው ነው ። ስለሆነም እንኩዋንስ በአፈሙዝ ዐይነቁራኛ ሥር የሚማቅቀው ህዝባችን ቀርቶ ራሱም አፈሙዙን የጨበጠው የመከላከያ ሠራዊት እንኩዋ የግንቦት 83 ተስፋው መንምኖ ፤ የበረከተ-መለስ ቅጥረኝነቱ እየተሰማው «ምን ይሻላል?» እያለ በሚቆዝምበት ወቅት ነው የነመለስ የ17ኛ አመት ድል ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪው የቀረበለት ። «አሻፈረኝ» ቢል ይፈረድበታል?

እንደ አጋጣሚ ሆኖ ደርጉ 17 አመታት ገዝቶ በወደቀበት 17ኛ አመት፤ ኢህአዴግ 17 አመታት ገዝቶ ወደበረከተ-መለስ የእብሪት ዘመን በተቀየረበት 17ኛ አመት ላይ ፤ ግንቦት ሰባት ንቅናቄን ማወጃችን ፤ ከደርጉ የ17 አመታት አገዛዝ እድሜ በላይ ይህ ግፈኛና ዘረኛ ሥርአት ተጨማሪ አንዲትስ ቀን እንኩዋ ሊሰጠው አይገባም ለማለትም ጭምር ነው ። በ17 አመታት የደርጉ ወታደራዊ ጭካኔና ፤ በ17 አመታት የበረከተ-መለስ ባለጌ ዘረኛ አገዛዝ የጎበጠው ትከሻችን «ከእንግዲህስ በቃን» እያለ ነው ። ሸክም ሲከብድ ማውረድ ተፈጥሮአዊ እንጂ ነው ። የምርጫ ጉዳይ አይደለምና ።

ሸክሙን ለማቅለል ብሎም ለማስወገድ ጫኞቹ የተሻለ አቅም አላቸው ። ተሸካሚው ሲመርረው አሽቀንጥሮ ከሚወረውር ይልቅ ፤ ጫኙ ርህራሄ ተሰምቶትም ሆነ ፤ ቢወረወር የሚደርስበትን ስብራትና መፈረካከስ ተረድቶ «ጎበዝ እስኪ ተጋግዘን ይህን ጭነት እናውርደው» ቢል እሰየው ነበር ። ግን እንዲህ አይነት ትሁትነት ከነበረከተ-መለስ ሰፈር ጭራሽ አልተሰምቶም ። ባንፃሩም የግፍ ቀንበር ሲጠነክር ወጊድ የማይል ህዝብ በአለም ታሪክ ፈፅሞ «አልታይቶም» እንላለን ። ውርድ ከራስ ነው ። በዘመናዊ ስልጠና ስም በኦጋዴን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ላይ ግብረሰዶም እንዲፈፅም የሚገደደው የመከላከያ ኃይል ሁኔታው አስመርሮት ፤ ልክ እንደ 1966ቱ የኔጌሌ ጦር ፤ አንዱ ሻለቃ እንኩዋን «ብካይ ይብቃ ፤ ውርደት ይብቃ!» የፈከረ ቀን ፤ የፍፃሜው መጀመሪያ መድፍ ይተኮሳል ። «የሰከረ አሳ» ላይ መረባረብ ባህሉ ያደረገው ኢትዮጵያዊ ትዕግስተኛ ፤ ወንዝ ወንዙን እያያዘ «አይዞህ ጎበዝ ! እህም ነው!» የደነከረ እንደሆን ፤ ማለቂያው አያምርምና ከዛሬው እንመካከር ፤ በክብ ጠረጴዛ ተቀምጠን በጨዋታው ህግ ላይ እንስማማ እንላለን ።

ጥያቄአችን ግልፅ ሃሳባችን ቀና ነው ። የመከላከያ ሓይሉና ፀጥታው ከገዢው ፓርቲ ይለዩ ፤ የዳኝነትና ሚዲያ ነፃነት ይከበር ፤ ህዝብ በነፃ በመረጣቸው እንደራሴዎቹ ይተዳደር ፤ የህዝቡንም ነፃ ምርጫ የሚያስተዳደር ነፃ የሆነ የምርጫ ቦርድ ይቋቋም ፤ እነዚህ ናቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄዎች ። ባለፉት 17 አመታት ሳደረሳችሁዋቸው ዕልቂቶች እንኩዋ መጠየቅ አለባችሁ ፤ በየማሌዥያውና ለንደኑ ላሸሻችሁት የህዝብ ጥሪት ሂሳብ አወራርዱ እንኩዋን አንልም ። የቀጣዮቹን አመታት የኢትዮጵያ ተስፋ ለማሳመር እስከተባበራችሁ ድረስ ወደሁዋላ ላናይ ፈቃደኛ ነን ነው የምንለው ። ይህ ዕድል ግን እስከ መጨረሻው እምቢ ብላችሁ በህዝቡና በሠራዊቱ መረባረብ ስትወድቁ የምታገኙት አይሆንም ። ያኔ በተራችሁ ቃሊቲ ይጠብቃችኋል ። በሞገደኝነታችሁ ለመቀጠል ከወሰናችሁ ከዛሬው የእስር ቤቱን አስተዳደርና አኗኗር ብታሻሽሉ ፤ ዞሮ መግቢያ ቤታችሁን የማደስ ያህል ነው ። የአጼ ኃይለ ሥላሴም ሆኑ የደርጉ ባለሥልጣናት እየተነሳ ያለውን የህዝብ ሞገድ ማየት አቅቷቸው ሳይሆን ለእስራትና ሞት የተዳረጉት፤ ከናንተ ባልተናነሰ እብሪት «ህዝብ የሚበላው እንጂ የሚገብረው አያጣም» እያሉ በውስኪ ሲራጩ መሆኑንም ማስታወስ ተገቢ ነው ። «የሰከረ አሳ መጣልህ»ን ባህሉ ያደረገ ህዝብ መረቡን መቼ ጥሎ እንደሚያሰግራችሁ ልታውቁት አይቻልምና ዛሬ ከተያያዛችሁት የድል ዳንኪራ ቀነስ ፤ ከእብሪቱ ተንፈስ ማለት ይበጃል እንላለን ።

ያለምክንያት አይደለም እንዲህ ማለታችን ። ፈረንጆች «ብዙ የተለወጠ በመሰለን ቁጥር በነበረበት ተጎልቶ ይገኛል» የሚሉት አይነት ምትሃት ነው ። ልክ ዛሬ በአበባ እርሻዎችና በመስተዋት ፎቆች እንዲሁም በሁርሶ «ዘመናዊ» ወታደራዊ ሥልጠናችሁ እንደምትመፃደቁት ሁሉ ፤ በ1966 አብዩት ዋዜማም በቦሎቄና ሰሊጥ እርሻዎች መስፋፋት እንዲሁም በማግና ቃኘው ወታደራዊ አማካሪዎች የሚመኩ ነበሩ ። «ፍፁም መረጋጋት» በሰፈነበት ቅፅበት ነው አምስት ሳንቲም የአውቶቡስ ዋጋ ጭማሪና 15 ሳንቲም የነዳጅ ዘይት ዋጋ ጭማሪ የየካቲትን አብዮት የለኮሰው ። የተቀየረ ነገር አይታየንም ። የተቀየረ ነገር ቢኖር ፤ የትግራይና ወሎ ረሃብ ወደ ደቡብ ዘምቶ በታሪኩ ለረሃብ ባእድ የሆነ ህዝብን ማጥቃቱንና ፤ ቢበዛ 300 ሺህ የነበረው የ1966 ረሃብተኛ ቁጥር ዛሬ በናንተ አገዛዝ በ10 እጅ መጨመሩ ብቻ ነው ። 17 አመታት ሙሉ ገበናችሁን የሸፈነላችሁ አሜሪካም ፤ በቆሎውን ሁሉ ወደ ነዳጅ ዘይት ለውጦ ገበያው በእህል ውድነት በተጨነቀበት ሰአት እንደ ጥንቱ ላይደርስላችሁ ስለሚችል ፤ ችግሩን የጋራ፤ መፍትሄውንም ብሄራዊና ሁሉን አቀፍ ለማድረግ የሚያስችሉንን የህዝብ ጥያቄዎች መመለሱ ይሻላል እንላለን ።

በመጨረሻም 17ኛ አመት የድል በአላችሁን ስታከብሩ የራሳችሁን ከበሮ ድምቀት ብቻ ሳይሆን እዚያኛውም መንደር ያለውን «ሽርጣም ሱማሌ» የካራ ፉጨት ማዳመጥ ይጠቅማል እንላለን ። የክልል ምርጫ በማሸነፋቸው ብቻ እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው እንደ አውሬ በመታደናቸው «እኛም ቤት እሳት አለ» ያሉ አማፂዎች በመሆናቸው ፤ ጀግንነት በደም የሚገኝ የጥቂቶች በረከት አድርጋችሁ እስካላያችሁ ድረስ ፤ ለነፃነቱ የሚሰንፍ እንዳይኖር የራሳችሁን ተሞክሮ ዋቢ አድርጋችሁ ብትቆዝሙበት ለራሳችሁም ለሃገርም ይጠቅማል እንላለን ። የ17ኛ አመት ድላችሁን ስታከብሩ በአርነት አውጪነት የጀመራችሁት ትግል ፤ በዘረኛ አውዳሚነት ተጠናቆ የታሪክ ተወቃሽ እንዳትሆኑ በፌስታውና ጓይላው መሃል ደክማችሁ አረፍ ስትሉ «የት ጀምረን የት ልንጨርስ ነው?» ብላችሁ ከራሳችሁ ጋር ብትነጋገሩ ተገቢ እንጂ ነው እንላለን ።

### መለስ ዜናዊ ከ300 በላይ ከሚሆኑ ከግብረሰናይ

ከእዚህም ጋር ተያይዞ በእዚህ ስብሰባ ላይ የአንዳንድ የግብረ ሰናይ ድረጅቶች ተወካዮች ያሳዩት አድርባይነት፣ህሊና ያለዉን ሰው የሚያሸማቅቅ ነበር። ከመለስ ዜናዊ ጋር በአካል ለመተያየት እድል ስላገኙ ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑ መሆናቸውን፣ የመለስ ዜናዊን ብልህ አመራር ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውና ግብረሰናይ ድርጅቶች በውጭ እጅ ይመራሉ፣ አጥፍተዋል ብለው ጠቅላይ ሚ/ሩ ካሰቡ በእርስዎ አመራር እንስተካከላን የሚል ንግግራቸው መብትን ለማስከበር ሳይሆን ለማደግደግና ጫማ ለመሳም በእዚህም የተነሳ በሌላዉ የመብት ኪሳራ የግል ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በስብሰባው መገኘታቸውን የሚገልጽ፣ ብዙሃኑን ያሳፈረና ያዋረደ ድርጊት እንደሆነ አንዳንዶቹ ተሰብሳቢዎች በቁጭት ሲገልጹ ተደምጠዋል።

ከሁሉ አሳፋሪ የነበረው መለስን የመሰለ አምባገነንና ነፍሰ ገዳይ ሲያወድሱ የታዩት ክብር-የለሽ ግለሰቦች ሳይሆኑ ቀደም ብሎ በተመሰሳይ ጉዳይ ላይ ከፍትህ ሚንስትሩ ጋር ውይይት በተደረገበት ወቅት ደ/ር ሚናስ ህሩይ ያቀረበውን ለምን የአብአዊና የዴመክራሲ መብት ተከራሪ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች አግዳችሁ ለእኛ የልማት ስራ ለምንሰራው ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች በነጻ የመንቀሳቀስ መብት አትሰጡም የሚለውን አሳፈሪ ሃሰብ ደጋግመው ያነሱ ተወካዮች በእዚህ ስብሰባ መታየታቸው ነው። ለግበረ ሰናይ ድርጅቶች ‹የድህነት ጌቶች› የሚል መጥፎ መጠሪያ ያተረፉላቸው እንዲህ አይነቶቹ ስግብግብ ግለሰቦች መሆናቸው ጥርጥር የለውም።

ቸው:: በከተማው የሚሰሩ መንገዶች ጉዳይ ብዙም የተወሳሰበ ነገር አይደለም:: በመንግስት ወጪ፤ መንግስት አንድም ከውጭ መንግስታት አለያም ህዝቡ ካስቀመጠው ገንዘብ በመበደር የሚሰሩ ናቸው::

በአጠቃላይ በአገሪቱ በተለይ ደግሞ በከተሞች ከዚህ በፊት በአገሪቱ ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት አለ:: ይህ የዋጋ ግሽበት በአነስተኛው ወደ 30 ከመቶ፤ ግን እንደ ነዋሪው ስሌት ከዚያም በብዙ እጥፍ (አንዳንድ ጊዜ በየሳምንቱ የሚጨምር) የበለጠ የዋጋ ጭማሪ በሁሉም አይነት ሸቀጦችና ግልጋሎቶች ላይ እየታየ ነው:: ይህ የዋጋ ግሽበት የፈጠረው የኑሮ ውድነት እንደ ኢትዮጵያ ያለ ድሀ አገር ላይ በብዙሀኑ ህዝብ ላይ የሚፈጥረው የኑሮ ቀውስ እጅግ አስከፊ ነው:: በብዙ የአገሪቱ ከተሞች ነዋሪው ህዝብ በእውነት እየተራበ መሆኑ የሚገርም አይደለም::

በጣም በሚገርም ሁኔታና ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ መጠን ሙስና ተስፋፍቶአል:: የሙስናው ደረጃ ከከፍተኛ ባለስልጣኖች አልፎ መሀከለኛ የፖለቲካና የቢሮክራሲ ካድሬ ጋር ደርሶአል:: ከዚህ ውስጥ ምንም በመንግስት ስራ ላይ ያልተሰማሩ፤ ከዚህ ቀደም የፖለቲካ ወይንም ወታደራዊ ካድሬ የነበሩ ሰዎች በ«ጉዳይ አስፈፃሚነት» ስም በቀጥታ በንግድ ውስጥ የተሰማራውን ጊዜኛ ከበርቴ በተለያየ ደረጃ ከሚገኙ የመንግስት ባለስልጣናት ጋር የሚያገናኘውና (ጠቀም ያለ ኮሚሽኑን በልቶ) የሙስና ቅብብሉን የሚያሳልጥ አዲስ አቀባባይ ከበርቴ ተፈጥሮአል::

እነኝህ ሶስት እውነታዎች የተለያዩ ይምሰሉ እንጂ በጣም የተገናኙ ናቸው:: **በተግባር እየሆነ ያለውም ምናልባት ከየካቲት 66 ዓ.ም የደርግ ንብረት ውርስ ወዲህ (የመሬት አዋጅ፤ የፋብሪካዎች ማገርና የከተማ ቤቶችን መውረስ) በጣም ከፍተኛው የንብረት ዝውውር በአገራችን አሁን እየተካሄደ ነው:: ይህ እንዴት እንደሆነ በአጭሩ ከማሳየቴ በፊት ግን በሁለቱ የንብረት ዝውውሮች መሀከል ያለውን አንድ መሰረታዊ ልዩነት ላስቀምጥ:: በ66 አብዮት ጊዜ የተደረገው የንብረት ዝውውር በገጠር ከመሬት ባለሀብቱ ተወስዶ መሬት ወደሌለው የቀድሞ ጭሰኛና መሬት የሌለው ድሀ ገበሬ፤ በከተማ ቦታና መሬት ውርስ ከአከራዮች ወደ ተከራዮችና የመንግስት ባለሙዋሎች፤ በፋብሪካዎች ደግሞ ከከበርቴው ወደ መንግስት በአጠቃላይ ግን በፊት ለፊትና በአዋጅ፤ ከጥቂት ባለሀብቶች ወደ ብዙሀን ድሆች የተደረገ የንብረት ዝውውር ነው:: የአሁኑ የንብረት ዝውውር በአዋጅና በፊት ለፊት የሚደረግ አይደለም:: ከዚያም በላይ የንብረት ዝውውሩ የሚደረገው ከድሀው፤ የተወሰነ ገቢ ካለው (ለምሳሌ ጡረተኛ) ወይንም ተራ ደሞዝተኛ፤ ከአነስተኛው ነጋዴና ገበሬ፤ ተወስዶ ንብረት ወይንም ትላልቅ ንግድ ወዳለው ሀብታም፤ ከዚህም ውስጥ በተለይ የመንግስት ድጋፍ ወዳለው የተወሰነ የሀብታም ክፍል ወይንም ሆን ተብሎ ወደሚፈጠር አዲስ የሀብታም መደብ መሆኑ ነው:: በሚገርም ሁኔታና ፍጥነት አጠቃላይ የአገሪቱ ሀብት እየተስፋፋ ሳይሆን ባለው ሀብት አዲስ የኢኮኖሚ ገዢ መደብ እየተፈጠረ መሆኑ ነው:: የንብረት ሽግግሩ ባጠቃላይ ከብዙሀኑ ወደ አናሳዎች ነው:: ስለዚህም ባለውና በሌለው መሀከል ያለው ልዩነት ሆን ተብሎ በሚያስፈራ ሁኔታ እየሰፋ ነው::** ይህ አዲስ ሁኔታ እንዴት እየተፈጠረ እንደሆነ በአጭሩና በቀላሉ ለዚሁ ተብሎ በግርድፉ በተዘጋጀ ምሳሌ ላስረዳ:: ምሳሌው ላይ ያለው ሂሳብ አጠቃላይ ቅኝቱን ለማሳየት በሚልና ስሌቱ እንዳይንዛዛ በጥቅሉ ነው የቀረበው::

ማንም እንደሚያውቀው አብዛኛውና በተለይ በትላልቅ የንግድና የኢንቬስትመንት ስራ ላይ የሚደረግ ወጪ ከባንክ በሚገኝ ብድር ነው:: በኢትዮጵያ ለሚደረግ ከፍተኛ ንግድ ወይንም ኢንቬስትመንት ባለሀብቱ 30 በመቶ ማቅረብ ከቻለ ባንኮች 70 ከመቶውን በብድር መልክ ይሰጣሉ:: መንግስትም ለሚያደርገው ማናቸውም እንቅስቃሴ ብር ሲያንሰው ከብሄራዊ ባንክ ተበድሮ ነው የሚሰራው:: ምንም እንኳዋን ባለሀብቶች ቢያንስ 30 ከመቶውን ማስቀመጥ ቢጠበቅባቸውም እሱንም ከኪሳቸው ለማውጣት ካልፈለጉ በሙስና (በጉዳይ አስፈፃሚዎች በኩል?) ከዚያም ያነሰ አውጥተው ብድሩን ያገኛሉ:: ስለዚህ አንድን የኢንቬስትመንት እንቅስቃሴ ለመጀመር ብዙ የግል ገንዘብ አያስፈልግም በተለይ ጥሩ ግንኙነቶች ካሉ:: በማስያዣነትም የሚያዘው ብዙውን ጊዜ ይኸው የሚሰራው ንብረት ነው:: ባንኩ የመንግስት ከሆነ ደግሞ የሚያስፈልገው ግንኙነት ከመንግስት ባለስልጣኖች ጋር ነው ማለት ነው::

ባንኮች በበኩላቸው እንዴት እንደሚሰሩና ትርፍ እንደሚያገኙ ይታወቃል:: ተራ ሰዎች ያላቸውን ገንዘብ በኪሳቸው ወይንም በፍራሻቸው ውስጥ ከሚያስቀምጡ ብራቸውን አነስተኛም ቢሆን ወለድ በሚያስገኝ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ያስቀምጣሉ:: ለዚህም ባንኩ የተቀማጭ ሂሳብ ወለድ (አሁን ላለፉት ብዙ አመታት 3 ከመቶ ነው) ይከፍላቸዋል:: ይህን ከህዝቡ የሰበሰበውን ገንዘብ ለተበዳሪዎች በከፍተኛ ወለድ ያበድራል (ይህ ደግሞ ወደ 8 ከመቶ አካባቢ ነው):: የባንኩ ትርፍ በሁለቱ መሀከል ካለው ልዩነት ላይ ወጪዎቹን ቀንሶ (የሰራተኛ ደሞዝ፤ የቤት ኪራይ...ወዘተ) የሚያገኘው ነው ማለት ነው:: ለምሳሌ አስቀማጮች በሙሉ አንድ ቢልዮን ብር ቢያስቀምጡና ከዚህ ውስጥ 800 ሚሊዮኑን ባንኮቹ ለደንበኛ ተበዳሪዎቹ ቢያበድሩ (ሁሉንም ሊያበድሩ አይችሉም የተወሰነውን አስቀማጮቹ ስለሚያወጡት) ባንኮቹ ለአስቀማጮች 30 ሚሊዮን በወለድ መልክ ይከፍላሉ:: ከተበዳሪዎቹ ደግሞ 64 ሚሊዮን ብር ይሰበስባሉ:: ከሁለቱ ልዩነት ከሚያገኙት 34 ሚሊዮን ብር ውስጥ ወጪአቸውን ችለው የሚተርፈው ትርፋቸው ነው ማለት ነው:: በዚህ ሁኔታ አስቀማጩም፤ ተበዳሪውም፤ አበዳሪ ባንኩም በተለያየ ደረጃ ይሁን እንጂ ሁሉም ይጠቀማሉ::

ይህ ምሳሌ ግን አሳሳች ነው:: ጊዜንና በጊዜ ውስጥ የሚፈጠረውን የብር የመግዛት አቅም ከግምት አያስገባም:: አንድ አስቀማጭ አንድ መቶ ብር ባንክ ሲያስገባ በአመቱ መቶ ብሩ 103 ብር ይሆንልኛል ብሎ አስቦ ነው:: አንድ ተበዳሪም በ8 በመቶ ወለድ ሲበደር የተበደረውን 100 ብር ሰርቶበትና አትርፎበት ከአመት በሁዋላ 108 ብር አድርጎ ለመመለስ ቃል ገብቶ ነው:: ምንም የዋጋ ግሽበት በሌለበት ሁኔታ የዛሬ አንድ ብር ወጋ ከአመት በሁዋላም የመግዛት አቅሙ ያው አንድ ብር ነው ማለት ነው:: የዋጋ ግሽበት ደግሞ የሚቀይረው ይህንን የብር የመግዛት አቅም ነው:: ለምሳሌ የዋጋ ግሽበት በአመት አስር በመቶ ቢሆን ያ አንድ መቶ ብር በባንክ ያስቀመጠው ሰው ከአመት በሁዋላ በጥሬው የሚያገኘው 103 ብር የመግዛት አቅሙ 92 ብር ከሰባ ሳንቲም ብቻ ይሆናል ማለት ነው:: አስቀማጩ ሰውዬ ከራሱ ገንዘብ ላይ 7 ብር ከሰላሳ ሳንቲም ከስሮአል ማለት ነው:: በአንፃሩ ተበዳሪው ለተበደረው 100 ብር ከአመት በሁዋላ የሚከፍለው 108 ብር የመግዛት አቅሙ ከዛሬ አንፃር ሲመዘን 97 ብር ከ 20 ሳንቲም ብቻ ነው:: ማለትም ይህ ተበዳሪ ከባንክ በመበደሩ ባንኩ በነፃ 2 ብር ከ 80 ሳንቲም ከፍሎታል ማለት ነው:: በእርግጥ ባንኩ ከራሱ ገንዘብ አይደለም የከፈለው:: ከዚያ ምስኪን 100 ብር እጠቀማለሁ ብሎ ካስቀመጠው ድሀ ነው:: ስለዚህ ዋና ተጠቃሚው ተበዳሪው ሲሆን ዋና ተጎጂው ደግሞ አስቀማጩ ነው ማለት ነው:: ከአስቀማጩ ወደ ተበዳሪው ንብረት እየተዘዋወረ ነው ማለት ነው:: የገንዘቡ መጠን በበዛ ቁጥር ደግሞ የተበዳሪው ጥቅም በዚያው ልክ እየጨመረ ይሄዳል ማለት ነው:: ከአስቀማጩና ከተበዳሪው ውጭ ያለው ሌላው ከእጅ ወደ አፍ የሚኖረው ህዝብ ደግሞ ከአስቀማጩም በላይ በኑሮ ውድነት እየተለበለበና እጅግ እየደኸየ ይሄዳል::

በሚቀጥለው ሳምንት ይቀጥላል